# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

ቁጥር 104 ግንቦት 5 ቀን 2002 ዓ.ም


አንብበው
ያስነብቡ!
አባዝተው
ያሰራጩ!

ምርጫን እንደመሰለያ መሳሪያ የሚጠቀመው ወያኔ በድህረ ምርጫ 97 በህዝባችን ላይ የፈጸመው አይነት ፋሽስታዊ ጭፍጨፋ እንዳይደገም ከተፈለገ ነጻ እና ገለልተኛ የሆነ የምርጫ አስፈጻሚ አካላት፤ ለሁሉም እኩል የሚያገለግል የሚዲያ አገልግሎት፤ ታማኝነታቸው ለህገመንግሥቱ ብቻ የሆነና ከፖለቲካ ወገናዊነት የጸዱ የፖሊስ፤ የመከላኪያና የደህንነት ተቋማት መመስረት ይኖርበታል።

ለወያኔ እድሜ መራዘሚያ ህጋዊና ሞራላዊ መሰረት እንዲያስገኝ ታስቦ በሚካሄድ ምርጫ መሳተፍ ለህዝባችን የሚያስገኘው ፋይዳ አይኖርም!!!

## በመድረክ ፓርቲ አባላት ላይ የሚደርሰው እንግልትና ግዲያ እንደቀጠለ ነው። በዚህ በያዝነው ሳምንት ሶስተኛ ሰው ተገድሏል

በሰሜን ሸዋ ዞን የመድረክ ፓርቲ አባል እና ቀስቃሽ የነበሩ ግለሰብ ሚያዝያ 26 ቀን በተኩስ መገደላቸውን ብሉምበርግ የተባለው የዜና ድርጅት የፓርቲው አመራር አባል የሆኑትን ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳን በመጥቀስ ዘግቧል።

እንደዜና ድርጅቱ ዘገባ አቶ ግርማ ካቤ የተባሉት ግለሰብ የመድረክ ፓርቲ ፖስተሮችን እየለጠፉ ሳሉ በጠራራ ጸሃይ ተተኩሶባቸው እንደሞቱ ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ ገልጸዋል። የአቶ ግርማ ግድያ ከየካቲት ወር መጨረሻ ወዲህ በመድረክ አባላት እና ደጋፊዎች ላይ ከተደረጉት እና ከተዘገቡት ህገ-ወጥ ግድያዎች ውስጥ ሶስተኛው ነው።

በየካቲት ወር ፍፃሜ ላይ በትግራይ ክልል የፓርቲው እጩ የነበሩት አቶ አረጋዊ ገብረዮሃንስ በአሰቃቂ ሁኔታ መገደላቸው ይታወሳል። በሚያዝያ ወር ደግሞ አቶ ቢያንሳ ዲባ የተባሉ እና ለፓርቲው ሲቀሰቅሱ የነበሩ ዜጋ በምእራብ ሸዋ በወያኔ ካድሬዎች በተደረገባቸው ድብደባ መሞታቸው በሰፊው ተዘግቦ እንደነበር ይታወሳል። በተመሳሳይ የጥቃት ዓላማ በጅማ ዞን የመድረክ አባል የሆኑ ግለሰብ የግድያ ሙከራ ተደርጎባቸዋል።

የወያኔ ባለስልጣናት እየተፈጸመ ያለውን ግድያ ከመካድም አልፈው ግለሰቦቹ የሞቱት በግል ጸብ ወይም በተፈጥሮ ህመም ምክንያት ነው በማለት ፍጹም ሃሰተኛ ማስተባቢያ መስጠትን ሆን ብለው እንደተያያዙት ለማወቅ ተችሎአል። የሃሰት ማስተባቢያቸውም ስሚ ያላገኘ መሆኑን ሲረዱም በተለይ የመድረክ ፓርቲ መሪዎች የድርጅታቸው (ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## በአዲስ አበባ ከተማ ገዢውን ፓርቲ እንደማይመርጡ በግልጽ የተናገሩ ሰዎች ድብደባ እየደረሰባቸው መሆኑ ታወቀ

በአዲስ አበባ ከተማ የወያኔ ካድሬዎች ከቤት ቤት እየተዘዋወሩ ነዋሪዎች በመጪው የምርጫ ተውኔት ማንን እንደሚመርጡ ሲጠይቁና መልስ እና አድራሻቸውን ሲመዘግቡ መሰንበታቸውን፤ ይህም ነዋሪዎችን ሲያሸብር እንደቆየ ከዚህ ቀደም በተደጋጋሚ መዘገባችን ይታወሳል።

በዚህ ሳምንት የደረሰን መረጃ ደግሞ፣ ወያኔን አንመርጥም ያሉ ሰዎች ድብደባ እየተፈጸመባቸው መሆኑን ያስረዳል። የግንቦት 7 ድምጽ ዘጋቢ ከአዲስ አበባ አጠናክሮ በላከው ዘገባ፣ ለደህንነት ሲባል ስማቸውን ለመግለጽ ያልተፈለገ አንድ ግለሰብ ለነዚሁ ካድሬዎች ወያኔን እንደማይመርጡ በግልጽ በመናገራቸው ክፉኛ ተደብድበዋል። እንደ ግለሰቡ ቃል፥ ጥያቄውን ያቀረቡላቸው ሰዎች መልሳቸውን ተቀብለው ከሄዱ ከሰላሳ ደቂቃ በኋላ ከዚህ ቀደም አይተዋቸው የማያውቋቸው ሶስት ሰዎች መጥተው ወደ ድብቅ ስፍራ በመውሰድ ድብደባ ፈጽመውባቸዋል።

የፊታችን ግንቦት 15 ቀን የሚደረገው የይስሙላ የምርጫ ተውኔት በተቃረበ ቁጥር፣ ዘረኛውና አምባገነኑ የወያኔ አገዛዝ በዜጎች ላይ የሚፈጽመውን እስከ ግድያ የደረሰ ሰቆቃ በስፋት አጠናክሮ ቀጥሎበታል።

## የዘረኛው ወያኔ አገዛዝ ባለስልጣናት አዲሱ ለገሰና ደመቀ መኮነን በቤንሻንጉል እና አማራ ክልሎች ያደረጉት ቅስቀሳ ያለስኬት ተጠናቀቀ

የወያኔ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስቴር አዲሱ ለገሰ እና የትምህር ሚንስትር ደመቀ መኮንን የሚመሩት ቡድን ፤በሚያዝያ ወር በቤኒሻንጉል እና በአማራ ክልል ከተሞች ቅስቀሳ ሊያደርግ ሄዶ በሃፍረት ተሸማቆ መመለሱ ታወቀ።

ከሚያዝያ 18 – 21 ቀን፣ በቤኒሻንጉል ክልል በድባጢ ከተማ እና በአማራ ክልል በዳንጓ ወረዳ በሚገኙ በዚገምና በቻግኒ ከተሞች ህዝቡ ለወያኔ ድምጹን እንዲሰጥ ለማግባባት ሁለቱ ባለስልጣናት የጠሩትን ስብሰባ የአካባቢው ነዋሪ ለመካፈል ፈቃደኛ አልነበረም። በዚህ ግራ የተጋቡት የአገዛዙ ባለስልጣናት የራሳቸውን ካድሬዎች እና የአገር ሽማግሌዎችን ለሚስጥር ስብሰባ የሚጋብዝ ደብዳቤ በማሰራጨት ህዝቡ ለወያኔ ድምጹን እንዲሰጥ እንዲያግባቡ ትእዛዝ ማስተላልፋቸውን የግንቦት 7 ድምጽ ዘጋቢ የአካባቢውን ሰዎች በመጥቀስ ዘግቧል። (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

ግዜ
ግንቦት 7 ዜና

## ዘረኛው የወያኔ አገዛዝ ህጋዊና ሰላማዊ የሆነው የመድረክ ፓርቲ አባላት ፖሊስ ገደሉ ሲል ወነጀለ

ዘረኛውና አምባገነናዊው የወያኔ አገዛዝ ህጋዊና ሰላማዊ በሆኑ ፓርቲዎች ላይ የሚያደርገውን ጥቃት እና ማስፈራሪያ በመቀጠል፣ ባለፈው ሳምንት የመድረክ አባላት አንድ ፖሊስ በጩቤ ወግተው ገድለዋል ሲል ወንጅሏል።

በኦሮምያ የወያኔ ፖሊስ የሰጠው መግለጫ፣ ቅዳሜ ሚያዝያ 30 ቀን በምእራብ ሸዋ ኢሉ ገላን ወረዳ ሃሰን ረጋሳ የተባለ የፖሊስ አባል በተደጋጋሚ በጩቤ በመወጋቱ እንደሞተ ገልጾ፤ ለዚህም ተጠያቂዎቹ የመድረክ አባላት ናቸው ብሏል። አገዛዙ ከአንድ ሳምንት በፊት በዛው በኦሮሚያ ክልል እጩው የሆነ ግለሰብ ስብሰባ ጨርሶ ሲወጣ በመድረክ ደጋፊዎች በተመሳሳይ ሁኔታ ተገድሏል ብሎ መወንጀሉ ይታወሳል።

መጪው የምርጫ ተውኔት በተቃረበ ቁጥር፣ በህጋዊው መድረክ ፓርቲ ላይ ጥቃቱን እያባባሰ የሄደው ወያኔ በአመራሩ ላይ የሚያደርገውን ማስፈራራት እና እንግልትም ቀጥሏል። ባለፈው ሳምንት ለብሉምበርግ ዜና ቃላቸውን የሰጡት ዶ/ር መረራ ጉዲና “ሁኔታው ጦርነት እንጂ ምርጫ አይመስልም” ብለዋል።

በህጋዊ መንገድ ብቻ በመታገል ለውጥ ለማምጣት እንችላለን ብለው ባመኑ ፓርቲዎች ላይ የተከፈተው ይህ ጦርነት፤ የወያኔን እውነተኛ ማንነት እስካሁን ላልተቀበሉ ሰዎች አይን ከፋች ነው ሲሉ ብዙ ተመልካቾች ይናገራሉ።

## በኦሮምያ ክልል በባሌ ዞን በአዳባ ከተማ በፈነዳ ቦምብ ሁለት ሰዎች መገደላቸው እና በርካቶች መቁሰላቸው ተዘገበ

ሐሙስ ሚያዝያ 28 ቀን በኦሮምያ ክልል አዳባ በተባለ ቦታ የኦህዴድ ስብሰባ በሚካሄድበት በተወረወረ ቦምብ ሁለት ሰዎች ሲሞቱ 14 መቁሰላቸውን አዣንስ ፍራንስ ፕሬስ የወያኔ ባለስልጣን የሆነውን ሽመልስ ከማልን በመጥቀስ ዘግቧል።

የወያኔ ሹምና የክልሉ ምክትል ፕሬዚደንት የሆነው አብዱላዚዝ ሙሃመድ በተገኘበት በዚህ ስብሰባ ላይ ቦምቡን ወርውረዋል ተብለው የሚጠረጠሩ ሶስት ግለሰቦች መታሰራቸው ታውቋል። ወዲያውኑም አገዛዙ ከሶስቱ አንዱ ከዚህ ቀደም በዲሲፕሊን ጉድለት የተባረረ ወታደር ነው ብሏል። አገዛዙ ለተፈጸመው ወንጀል ከወትሮው በተለየ ሁኔታ የትኛውንም ቡድን በፍጥነት ከመወንጀል ለጊዜው ተቆጥቧል።

የወያኔ አገዛዝ ከሁለት ሳምንታት በፊት በትግራይ ክልል የተከሰተውን የቦምብ አደጋ፣ በተፈጸመ በጥቂት ሰዓታት ውስጥ በኤርትራ ላይ መወንጀሉ ይታወሳል። በዚህ ሳምንት ከአሜሪካ ድምጽ ሬድዮ ጋር ቃለ መጠይቅ ያደረገው የወያኔ ባለስልጣን ቴዎድሮስ ሃጎስ ደግሞ ጥቃቱን ያደረሰው የትግራይ ህዝብ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ የተባለው ድርጅት ነው ሲል ውንጀላውን አሻሽሎታል።

## የዘረኛው የወያኔ አገዛዝ ፌዴራል ፖሊስ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ላይ ዘር የለየ ድብደባ መፈጸሙ ታወቀ

ባለፈው ሳምንት በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በስድስት ኪሎ ግቢ በተነሳውና የሁለት ተማሪዎችን ህይወት ቀጥፎ በርካቶችን ባቆሰለው ረብሻ ሰበብ ወደ ግቢው የገባው የወያኔ ፌዴራል ፖሊስ ተማሪዎችን በዘራቸው በመለየት ድብደባ መፈጸሙ ታወቀ።

የግንቦት 7 ድምጽ ዘጋቢ ከአዲስ አበባ በላከው መረጃ የፌዴራል ፖሊሶች የተነሳውን ረብሻ በማብረድ ስም ወደ ግቢው ከገቡ በኋላ የተማሪዎችን መታወቂያ እያዩ ኦሮሞ ሆነው የተገኙትን ክፉኛ ደብድበዋል። በዚህ እና በረብሻው ወቅት በነበረው ድብድብ የተጎዱ በርካታ ተማሪዎች ወደ ሆስፒታል መወሰዳቸውም ታውቋል። (ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## ከሳምንታት በፊት በወያኔ ካድሬዎች የተገደሉት የመድረክ ቀስቃሽ አቶ ቢያንሳ ዲባ በድብደባ መሞታቸውን የወረዳው ፖሊስ አረጋገጠ

የኦሮሞ ህዝብ ኮንግረስ (ወይም አህኮ) ፓርቲ ቀስቃሽ የነበሩት እና ከሶስት ሳምንታት በፊት ለህልፈተ ህይወት የተዳረጉት አቶ ቢያንሳ ዲባ በደረሰባቸው ድብደባ መሞታቸውን ከክልሉ ፖሊስ ጋር በመቃረን የወረዳው ፖሊስ ማረጋገጡ ታውቋል።

በቅርቡ የደረሰን መረጃ እንደሚያመለክተው፣ የድብደባው ወንጀል በተፈጸመበት ስፍራ ቀድመው የተገኙት የወረዳው ፖሊሶች አቶ ቢያንሳ ስለመደብደባቸው ቃል ሰጥተው ነበር። ይኸው ቃላቸውም ከሁለት ሳምንታት በፊት የኦሮምያ ፖሊስ ኮምሽን ምክትል ኮምሽነር ደመላሽ ገብረሚካኤል በቴሌቪዥን መስኮት ቀርቦ አቶ ቢያንሳ በድብደባ መሞታቸውን በሚክድበት ወቅት በስህተት በቴሌቪዥን ተቀርጾ ታይቷል።

የወያኔ አገዛዝ አቶ ቢያንሳ ዲባ ምንም ድብደባ እንዳልተደረገባቸው እና የሞቱት በተፈጥሯዊ ሁኔታ እንደሆነ ከመናገር አልፎ፤ ከዚህ ጋር የማይስማሙ የመድረክ አመራር አባላትን፣ በተለይም አቶ ቡልቻ ደመቅሳን፣ እንደሚከስ ዝቷል። (ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## ግርግር 2002 ትኩረታችንን እንዳያዛባ - ጠንቀቅ!!!

ኪስ አውላቂዎችም የራሳቸው "ልሂቃን" አላቸው። እነዚህ በመሰሪ ችሎታዎቻቸው የላቁ ኪስ አውላቂዎች በአስደናቂ "ጥበብ" ከመስረቅም አልፈው የሰረቁትን ሰው በሌብነት አስጠርጥረው ማስደንገጥ፣ ማዋከብና ማስደብደብ ይችላሉ። እነዚህ መሰሪዎች የዋሁን ተበዳይ "ሌባ" አሰኝተው እነሱ ጨዋ መስለው መታየት ያውቁበታል። ኪስ ውስጥ ሲገቡ ያየ ሌላ ሰው ካለ እሱንም ጭምር በሌብነት ከማሳጣት አይመለሱም። ይኸንን ውጤት ለማግኘት ከሚጠቀሙባቸ መንገዶች አንዱና ምናልባትም ዋነኛው ግርግር ማስነሳት ነው። በግርግሩ ውስጥ ራሳቸውን ህግ አስከባሪ አድርገው በመሾም በድብቅ የሰረቁትን ሰው በገሃድ ሊደግሙት ይችላሉ። ይኸ ችሎታቸው ነው የሌቦች የበላይ ያደረጋቸው። እነሱም በዚህ ችሎታቸው ይኩራራሉ፤ እንደ ጀብድም ያወሩታል።

ወያኔ በምርጫ ዘረፋ "ጥበብ" ተመሳሳይ የብቃት ደረጃ ላይ ደርሷል። ይህንን የላቀ የሌብነት ችሎታውን በምርጫ 97 ማግሥት በተግባር ላይ አውሎታል። ተቃዋሚዎች "ወያኔ ድምፅ ዘረፈን" በማለት አቤቱታ ሲያቀርቡ፤ ወያኔ ደግሞ "ተቃሚዎች ድምፅ ዘረፉኝ" ሲል አማረረ። ከብዙ ውዝግብ በኋላ ከተከራካሪ ፓርቲዎች አንዳንድ ሰው እና ከምርጫ ቦርድ አንድ ሰው ያለበት ኮሚቴ ይፍረደው ተባለ። ወያኔ በሁሉም ክርክሮች ሁለት ለአንድ በሆነ የድምፅ ብልጫ "እያሸነፈ" ከቀድሞው ተጨማሪ ወንበሮችን አገኘ። ቀጥሎም ግርግር አስነሳና ተቀዋሚዎችን ሰብስቦ አስሮ በእነሱም፣ በሕዝብም፣ በፍትህም ላይ በግላጭ ተሳለቀ። ይህ ነው የረቀቀ ሌብነት!!! ምርጫ 97 ካሳወቀን በርካታ መራር ሃቆች አንዱ ነፃ ተቋማት በሌሉበት በተበዳዮች አቤቱታ ጉልበተኛው በዳይ የሚጠቀም መሆኑን ነው።

የ1997ቱ የምርጫ ዘረፋ ታሪክ በዚህ ብቻ አላበቃም። ወያኔ በገለልተኝነት ምርጫውን የታዘበውን የአውሮፓ ኅብረት የምርጫ ታዛቢዎች ቡድንን በተለይ የቡድኑን መሪ የተከበሩ ወ/ሮ አና ጎሜዝን ከተቃዋሚዎች ጋር አዳብሎ ከሰሳቸው፣ ስማቸውንም አጠፋ። አገራዊ ነፃ የምርጫ ተቋማት ከሌሉ ገለልተኛ የውጭ ታዛቢዎች ቢኖሩም እንኳም የሕዝብን ድምፅ ማስከበር እንደማይችሉ ምርጫ 97 አሳይቶናል።

በከተማ አውቶቡሶች ውስጥ የሚያጋጥመን ዓይነት ግርግርን የመጠቀም ኪስ አውላቂነት በምርጫ 97 ማየታችን እውነት ነው። ይህ ንጽጽር የወያኔን ማንነት ብቻ ሳይሆን የወያኔ ምርጫ ምንነትንም በሚገባ ይገልፃል ብለን እናምናለን።

ዘንድሮ ወያኔ "የመጠቀ" የሌብነት ችሎታውን ከምርጫው አስቀድሞ ሥራ ላይ እያዋለው ነው። ተቃዋሚዎች መዋከባቸው፣ መደብደባቸውና መገደላቸው ለኢትዮጵያና ለዓለም ሕዝብ ማሳወቃቸውን ተከትሎ ወያኔ የተበዳዮችን ጩኸት ቀምቶ እሪታውን እያቀለጠው ነው! ወያኔ በከፍተኛ ድምፅ "ደጋፊዎቼ ተደበደቡብኝ"፣ "ቦንብ ተወረወረብኝ"፣ "ፓሊስ በስለት ተወግቶ ተገደለብኝ" እያለ ነው። የወያኔ ጩኸት ከእውነተኛ ተበዳዮቹ እሮሮ በላይ እንዲሰማ የሚዲያ ተቋማቱ እየተጉ ናቸው። ሆኖም ግን አንዳንድ ነገሮች የተዘበራረቀባቸው ይመስላል።

የወያኔ ሚዲያ በአንድ በኩል ወያኔን ተጠቂና ተበዳይ አድርጎ ለማቅረብ ሲሞክር በሌላ በኩል ደግሞ "ከኮማንድ ፖስቶች" በሚወጡ መግለጫዎች አማካይነት ወያኔን ጡንቸኛ አድርጎ ለማቅረብ ይሞክራል። እነዚህ ሁለቱ ሚናዎች አብረው አልሄድ ብለውት ወያኔ ችግር ውስጥ ገብቷል። የኢትዮጵያ ሕዝብ ለወያኔ ምርጫ ደንታ ያልሰጠ በመሆኑ እና ተፎካካሪዎቹም ቢያንስ በ97 የነበራቸውን ያህል ጥንካሬ የሌላቸው በመሆኑ የምርጫ ጨዋታውን ለማሟሟቅ ወያኔ ሁለቱንም ሚናዎች ራሱ መጫወት ግድ ሆኖበታል። ለምርጫው ማሟሟቂያነት በአዲስ አበባ ከተማ ብቻ ሶስት ሺህ የስለላ ቡድኖችን ማሰማራቱም ሁኔታዎችን ከማመሰቃቀሉ በስተቀር የፈየደው ነገር የለም። እንዲያውም ሰላዮቹ ነዋሪዎችን ከማስመረር አልፈው እርስ በርስ የጎሪጥ መተያየት ጀምረዋል እየተባለ ነው። ወያኔ የተበዳይነትም የጉልበተኝነትም ሚና ለመጫወት የሚያደርገው ጥረት የዘንድሮዉን የምርጫ ተውኔት አመሰቃቅሎታል።

ይሁን እንጂ የወያኔን የምርጫ ተውኔት ያባባሰው ምስቅልቅል አገራችንን ወደ ባሰ አደጋ እየገፋት ይገኛል። ግፍ ሲበዛ አመፅ በየትና እንዴት እንደሚገነፍል መገመት ከባድ ነው። በእንዲህ ዓይነት ምስቅልቅል ወቅት የሚፈነዱ አመፃዎች በቀላሉ ከቁጥጥር ውጭ ሊወጡ ይችላሉ። ሰሞኑን በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ ኦሮሚያና ትግራይ ውስጥ እያየናቸው ያሉት አሳዛኝ ሁኔታዎች የዚህ እውነታ አመላካቾች ናቸው።

ታድያ ይህ ሁሉ እየሆነ ያለው በቅድመ ምርጫ ወቅት መሆኑንም ልብ ልንል ይገባል። የወያኔ አጭበርባሪዎች ለምርጫው ቀን እና ለድህረ-ምርጫ ያቆዩልን ምንድነው? ይህስ በግርግር የመጠቀም "ጥበባቸው" ኢትዮጵያችንን ወደየት ይወስዳት ይሆን? እነዚህ እኛን በእጅጉ የሚያሳስቡን ጉዳዮች ናቸው።

በእኛ እምነት ለአብዛኛው የኢትዮጵያ ሕዝብ ምርጫ 2002 የሚባል ነገር የለም። ያለው ግርግር 2002 ነው። ምርጫ ሳይኖር ሊዘረፍ ስለሚችል የሕዝብ ድምፅ አናወራም። ይልቁንስ "ምርጫ 2002" የተሰኘው ድራማ የሚያስነሳው ግርግር 2002 በአገራችንና ሕዝባችን ላይ ጉዳት ለማድረስ የተዘጋጁ ሌቦችን ይጠቅማልና እንጠንቀቅ።

አገራችን በተራ ሌቦችና አጭበርባሪዎች መዳፍ ውስጥ በመውደቋ አበሳችን የበዛ መሆኑ ግልጽ ነው። ይህ ሁላችንንም ሊያበሳጨን ይገባል። ይህ የምርጫ ድራማና ተያይዞ የመጣው ግርግር ትኩረታችንን አናግቶ፤ እርስበርሳችንን አናቁሮ የወያኔ ሲሳይ እንዳንሆን እንጠንቀቅ።

ሌቦች ግርግር ሲያስነሱ ኪስን መጠበቅ ብልህነት እንደሆነ ሁሉ ወያኔ በሚያስነሳው የምርጫ ተውኔትና ግርግር ምክንያት ትኩረታችን እንዳይዛባ መጠንቀቅ የሁላችንም ኃላፊነት ነው እንላለን።

**ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!!!**

### በመድረክ ፓርቲ አባላት ላይ የሚደርሰው እንግልትና . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

አባል እነደነበሩ በእርግጠኝነት የሚመሰክሩላቸውንና የተገደሉትም ለፓርቲያቸው የምርጫ ዘመቻ በማድረጋቸው እንደሆነ የሚያረጋግጡላቸውን አቶ ቢያንሳ ዳባን፣ የወያኔ አባል ነበሩ በማለት እስከመከራከር መድረሳቸውን ለመታዘብ ተችሎአል።

የአቶ ግርማ ካቤን ግድያ አስመልክቶ ሰሞኑን ለሮይተርስ የዜና አገልግሎት ቃሉን የሰጠው የወያኔ ኮሚኒኬሽን ሃላፊ ዋሾው በረከት ስምኦን፤ ያንኑ የተለመደ ክደት በመድገም፤ ግለሰቡ የተገደሉት በግል ጸብ ምክንያት እንደሆነና የመድረክ አባልም እንዳልነበሩ ተናግሯል። ወያኔ ለስልጣን ዕድሜው መቀጠል ምንም የሚያሳስበው የምርጫ ሂደት በሌለበት እራሱ ብቻ በሚፈነጭበት ባዶ ሜዳ ለምን ንጹሃን ዜጎችን እንደሚገድልና እንደሚያሰቃይ የተጠየቁት አንድ የፖለቲካ ተንታኝ፤ በምርጫው ለመሳተፍ እየተንቀሳቀሱ ያሉ አንዳንድ ተቃዋሚ ሃይሎች ምናልባትም ወያኔ በውዴታ ለመልቀቅ ባላሰበባቸው አንዳንድ የትግራይና አዲስ አበባ የምርጫ ክልሎች የመሸነፍ ዕጣ ከገጠመው እንደተለመደው የምርጫውን ውጤት ከማጭበርበር ወደኋላ የማለት ፍላጎት ስለሌለው ድርጊቱን ተከትሎ ሊነሱ የሚችሉትን ውዝግቦች በመፍራት ከወዲሁ ህዝቡንና ተቃዋሚ ፓርቲዎቹን በፍርሃት ለማሸማቀቅ ታስቦ የሚወሰድ እርምጃ ነው በማለት አስተያየታቸውን ሰጥተዋል።

### የዘረኛው የወያኔ አገዛዝ ፌዴራል ፖሊስ በአዲስ አበባ . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

በተያያዘ ዜና፥ የወያኔ ፌዴራል ፖሊስ ተመሳሳይ ረብሻዎች በሌላ ዩኒቨርሲቲዎች እንዳይከሰቱ ለማስቆም በሚል ሰበብም በአገሪቱ ዙሪያ ወደሚገኙ አንዳንድ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት መግባቱን ዘጋቢያችን የላከው መረጃ አስረድቷል። በ1997ቱ ምርጫ ማግስት የወያኔ የደህንነት ሃይሎች ወደ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በመግባት እና ሆን ብሎ በተደረገ ትንኮሳ ረብሻ ከቀሰቀሱ በኋላ፣ በማረጋጋት ስም ተማሪዎችን ክፉኛ መደብደባቸው እና ማሰራቸው ይታወሳል። (ይቀጥላል) ⟶

ቅዳሜ ሚያዝያ 23 ቀን በስድስት ኪሎ ግቢ የተቀሰቀሰውና ለቀናት የዘለቀው ይህ ረብሻ ከኦሮምያ የመጡ ሶስት ተማሪዎች ተንቃሳቃሽ ስልኮች በመጥፋታቸው የተጀመረ ቢሆንም፤ ባጭር ጊዜ ውስጥ ወደ ቡድን እንዲሁም ወደ ዘር ጸብ መሻገሩን ዘግበናል። ተማሪዎቹ የንብረታቸውን መጥፋት ለግቢው ፖሊስ ሊያመለክቱ ሲሄዱ፣ ከኦሮምያ መሆናቸው እንደታወቀ፤ ምርጫውን ልታስተጓጉሉ እንጂ እውነት ስልክ ስለጠፋባችሁ አይደለም በሚል መወንጀላቸው እና ለእንግልት መዳረጋቸው ችግሩን አባብሶታል።

### ከሳምንታት በፊት በወያኔ ካድሬዎች የተገደሉት . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

የአቶ ቢያንሳ ዲባ አባት የሆኑት አቶ ዲባ ጋዲሳ ባለፈው ሳምንት ለአሜሪካ ድምጽ ራድዮ በሰጡት ቃል ልጃቸው የኦሮሞ ህዝብ ኮንግረስ ፓርቲ ደጋፊ እንደነበሩ እና የሞቱትም የወያኔ ሚሊሻ አባላት ባደረጉባቸው ድብደባ እንደሆነ መስክረዋል። በተጨማሪም፣ የአቶ ቢያንሳ ዘመድ የሆኑት አቶ ዳርጊ መረራ፣ ሟች አቶ ቢያንሳ ህክምና ሲወስዱ በቆዩበት ጥቁር አንበሳ ሆስፒታል የተወሰደ እና ክፉኛ መደብደባቸውን የሚያሳይ የኤክስሬይ ምርመራ ውጤት በእጃቸው እንደሚገኝ ለአሜሪካ ድምጽ ሬድዮ አስታውቀዋል። አቶ ዳርጊ የኤክስሬይ ምርመራ ውጤቱን ከወሰዱ በኋላ ፖሊስ ሊይዛቸው ሞክሮ እንደተኮሰባቸው፤ ነገር ግን ባሁኑ ሰዓት ተደብቀው እንደሚገኙ ገልጸዋል።

በወያኔ አገዛዝ ስር ግለሰቦችን ለመወንጀል የፈጠራ ሰነዶችን ማቅረብ እና የሃሰት ምስክሮችን ማቆም የተለመደ ተግባር መሆኑ ይታወቃል። አርቲስት ቴዎድሮስ ካሳሁን ሰው ገድለሃል በሚል ክስ ታስሮ ወደ ወያኔ ፍርድ ቤት በሚመላለስበት ወቅት፣ አቃቤ ህጉ እንደ መረጃነት ፍርድ ቤት ካቀረባቸው ሰነዶች ውስጥ አንዱና በሃኪሞች የተፈረመበት የአስከሬን ምርመራ ውጤት፤ ሟች የሞተበት ቀን ተከሳሹ አገር ውስጥ ባልነበረበት ቀን እንደሆነ ማሳየቱ ይታወሳል። በወቅቱ ይህ ለወያኔ የፍርድ ቤት ጉዳይ አስፈፃሚዎች አሳፋሪ የነበረ ሲሆን፤ ሆስፒታሉ የፈጸመው ስህተት ነው በማለትም ቀኑን ማስቀየራቸው ይታወሳል።



**የፖስታሳጥን ቁጥር ፦** POBox: 4916
2003EX Haarlem, The Netherlands

ሃይለ ሀሳብ

የግንቦት 7 ድምጽ፤ ቁጥር 104 ግንቦት 5 ቀን 2002 ዓ.ም፤

# እስከዛሬ ድርጅቶቻችን ውጤታማ ለምን አልሆኑም? ግንቦት7ስ በምን ይለያል?

ታደሰ ብሩ አፕሪል 10 2010 ሙኒክ ላይ በተካሃደ ህዝባዊ ስብሰባ የቀረበ ንግግር (ክፍል 2 ካለፈው የቀጠለ)

## ክብራትና ክቡራን

ከላይ በአጭሩ እንደገለጽኩት ድርጅቶችን ሲበጥበጡና ሲያፈርሱ የቆዩ መሠረታዊ ምክንያቶች በአምስት ዋና ዋና ክፍሎች መመደብ ይቻላል።

1. የግለሰብ አባላት በተለይም የፓርቲ መሪዎች ተክለ ሰውነትን / personality/ የተመለከቱ ጉዳዮች፤
2. የአባላት የእርስ በርስ ግኑኝነት ማለትም የሳይኮ-ሶሻል ጉዳዮች፤
3. የድርጅቱን ርዕይ፣ ተልዕኮና ግብ የተመለከቱ ጉዳዮች፤
4. የድርጅቱ ደንቦች፣መርሆዎችና አፈፃፀማቸውን የተመለከቱ ጉዳዮች፤ እና
5. የውጭ ግኑኝነት ማለትም ድርጅቱ ከሌሎች ድርጅቶች ጋር ሊኖረው ስለሚገባው ግኑኝነት በተመለከተ የሚነሱ ቅራኔዎች ናቸው።

በጣም በአጭሩ እያንዳንዱን በየተራ እንድናያቸው ፍቀዱልኝ።

### 1. የግለሰቦች የስብዕና ችግር

ግንዛቤ /perception/ ከእውነታ /fact/ በላይ የሚሆንበት ጊዜ አለ። ሰዎች ነጬን ነገር ጥቁር ነው ብለው ካመኑ ማስረጃ አይመልሳቸውም። የሰዎች ግንዛቤ በብዙ ምክንያቶች ሊዛባ ይችላል። እድሜ፣ የሥራ ጫና፣ ወከባ፣ አሉባልታ፣ ሃሜት፣ ውሸት፣ ጥቅማ ጥቅሞች እና የማመዛዘን ችሎታ ማጣት የግንዛቤ አቅምን ያዳክማሉ። አካባቢያችን በግንዛቤዓችን ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ አለው። ሰዎች በተዛባ ግንዛቤ መነሻነት የሚወስዱት አቋም በድርጅቱ ላይ ከፍተኛ ኪሳራ ሊያደርስ ይችላል። በተለይ ግለሰቡ የድርጅቱ መሪ ከሆነ ጉዳቱ እጅግ ከፍተኛ ይሆናል።

ኢትዮጵያ ውስጥ የፓለቲካ ድርጅቶች ከራሳቸው ስም ይልቅ በመሪዎቻቸው ስም ይታወቃሉ። ብዙዎቹ የእከሌ ፓርቲ እየተባሉ ይጠራሉ። ድርጅቱ እንደ መሪው ሁሉ ብሔር (ወይም ብሔረሰብ)፣ እድሜ፣ የትምህርት ደረጃ ... ወዘተ ይኖረዋል። ድርጅቱ እንደ መሪው ሁሉ ባህሪም ይላበሳል። አንዳንዱ ድርጅት ቁጡ ነው፤ ሌላው መሰሪ። አንዳንዱ ችኩል፣ አንዳንዱ ቀርፋፋ ነው። ይህ ሁሉ ነገር ውሎ አድሮ በድርጅቱ ውስጥ ቅሬታን መፍጠሩ እና በጊዜው የእርምት እርምጃ ካልተወሰደበት ደግሞ አንድ ቀን መፈንዳቱ አይቀርም።

### 2. የአባላት የእርስበርስ ግኑኝነትን በተመለከተ

የአባላት የእርስበርስ ግኑኝነቶች የቅራኔዎች ምንጭ የሚሆኑባቸው በርካታ ምክንያቶች ቢኖሩም ሶስቱን ብቻ ልጥቀስ

#### 2.1 የጌታና ሎሌ ግኑኝነት

*መንግሥቱ ኃይለ ማርያም እንደምን አምባገነንነትን "እንደተለማመደ" ዳዊት ወልደጊዮርጊስ የሚከተለውን በመሰለ አገላለጽ አብራርቶልናል።*

> *በመጀመሪያ እሱም ሻለቃ እኛም ሻለቃ ነንና እጃችንን እኪሳችን ዉስጥ ከተን እናወራ ነበር። ሳናውቀው እጃችን ከኪሳችን ወጣ። አሁንም ሳናውቀው እጃችን ወደኋላ ዞረ። ሳናውቀው "ጓድነትዎ" ማለት ጀመርን .... እሱ ምንያድርግ?*

በአብዛኛዎቹ የኢትዮጵያ ፓርቲዎች ውስጥ የአባላት እኩልነት በወረቅትና በወሬ ብቻ ነው ያለው። ግኑኝነቶች በአመዛኙ የጌታና የሎሌ አይነት ናቸው። ስለዚህ በአንድ በኩል ጌቶችና ታማኝ ጋሻ ጃግሬዎች፤ በሌላ በኩል ደግሞ አማጺያንና አልቃሾች ተፋጠዋል።

#### 2.2 ዘረኝነት

ዘረኝነት የወያኔና ሌሎች በዘር የተደራጁ ድርጅቶች ችግር ብቻ አይደለም። ኢትዮጵያ ውስጥ ዘረኝነት ህብረብሄራዊ ነን የሚሉ ፓርቲዎችም ችግር ነው። ብዙ ፓርቲዎች በጣም ረቂቅ በሆነው የዘር የውስጥ ፓለቲካ ምክንያት ተተኪ መሪዎችን ማፍራት አልቻሉም።

#### 2.3 የመሪዎች ፉክክር

አንዳንድ ድርጅቶች በይፋ ከሚታወቀው መሪ በተጨማሪ ሌላ በይፋ የማይታይ መሪ አላቸው። ሁለቱ መሪዎች ተፎካካሪ ከሆኑ ሁለት የንብ አወራዎች በአንድ ቀፎ ውስጥ መኖር እንደማይችሉ ሁሉ እነሱም ድርጅቱን በትነው የየድርሻቸውን ይዘው ሊጓዙ ይችላሉ። ሁለቱ መሪዎች ተደጋጋፊ ከሆኑና በይፋ የማይታወቀው መሪ በይፋ ከሚታወቀው መሪ በላይ ተሰሚነት ያለው ከሆነም ድርጅቱ ለቅራኔ ቅርብ ነው።

### 3. የድርጅቱ ርዕይ፣ ተልዕኮና ግብ በተመለከቱ የሚነሱ ቅራኔዎች

ግልጽ የሆነ ርዕይ፣ ተልዕኮና ግብ አለማስቀመጥ ድርጅትን የንትርክ ቤት ያደርጋል። አንዳንድ ድርጅቶች ምን እንደሚፈልጉ በውል ሳያውቁ ሲቀር ይህንን ድክመታቸውን የሚሸፍኑት አባሎቻቸውን ስሜታዊ በሆነ እምነት በማጥመቅ ነው። ቀደም ባሉት ዓመታት ብዙ ኢትዮጵያዊ ድርጅቶች ማርክሲዝም፣ ሌኒኒሲዝም፣ ማኦኢዝምን ለዚህ ዓላማ ተጠቅመዋል። እነዚህ እምነቶች ለጥያቄዎች ሁሉ የማያወላዳ ምላሽ ስላላቸው "ወደፊት ምን ዓይነት ኢትዮጵያን መፍጠር እንፈልጋለን?" በሚለው ጥያቄ ራሳቸውን ማስጨነቅ አላስፈለጋቸውም። በወቅቱ ከነበሩት ድርጅቶች ወያኔ በእጅጉ ይለያል። ወያኔ የአማራ ጥላቻ (በተለይም የሸዋ አማራ ጥላቻ) የእምነቱ ምሰሶ አድርጎ ነው የተነሳው። እርግጥ ነው እሱም እንደ ሌሎቹ ማኦኢዝምና ስታሊኒዝም ሰብኳል፤ አሁን ደግሞ አብዮታዊ ዲሞክራሲ እና ልማታዊ መንግሥት ስለሚባሉ ነገሮች ያነበንባል። ይሁን እንጂ እነዚህን ለሕዝብ ግኑኝነት ሥራዎች የሚገለገልባቸው ጭምብሎቹ ናቸው። ወያኔ ትንሽ ችግር ውስጥ በገባ ቁጥር ጭንብሉን አሽቀንጥሮ ወደ ትምክህተኛ አማራ ትንታኔው ይመለሳል። ለምሳሌ ሰሞኑን እነስዬ አብርሃን የሸዋ አማራ ቅጥረኞች በማለት የሚኮንኑው ጽሁፍ አይጋ ፎረም ላይ ታገኛላችሁ። እሱ ነው የወያኔ ዋነኛ አቋም ማለት። የመለስም ዜናዊ የመቀሌ ንግግሩ መሠረትም ይኸው ነው።

ሌሎችም በርካታ የኢትዮጵያ የፓለቲካ ስብስቦች የርዕይ ቀውስ ሲገጥማቸው ብሶትን መቀስቀስ አማራጫቸው ይሆናል። አክራሪ እምነቶችም የርዕይ ቀውስ መሸፈኛነት የሚውሉበት አደጋም አለ። ይህ አካሄድ ስሜታዊ ከመሆኑ በላይ የሚቀሰቅሰው የድርጅት ውስጥ ቅራኔ እጅግ አደገኛ ነው።

### 4. የድርጅት ደንቦችና መመሪያዎች እና አፈፃፀማቸው

በድርጅቶች ውስጥ የሚነሱ ቅራኔዎች ከድርጅቱ ደንቦችና መመሪያዎች ጋር ተዛምዶ አላቸው። በአንድ በኩል ደንቦች ራሳቸው የቅራኔ ምንጭ ሊሆኑ ይችላሉ። ለምሳሌ አባላት አንድን ደንብ በማጽደቅና ባለማጽደቅ ሊጣሉ ይችላሉ። በሌላ በኩል ደግሞ ተደንግጎ ተቀባይነት ያገኘ ደንብም የቅራኔ ምንጭ ሊሆን ይችላል። ለምሳሌ "ደንብ ጥሳችኋል"፤ "የለም እኛ አይደለንም እናንተ ናችሁ የጣሳችሁት" በመባባል እንደሚበጣበጡት ማለት ነው። ቅራኔ ውስጥ የገቡ አንጃዎች የድርጅቱን ደንብ ማጣቀሳቸው መቼም የማይቀር ነው። ደንቦች ሥርዓት ማስያዣ መሆን ሲገባቸው የቅራኔ ምንጭ የሚሆኑበት አጋጣሚ በርካታ ነው።

### 5. የውጭ ግኑኝነትን በተመለከተ

አንዳንድ ድርጅቶች ወዳጅና ተፎካካሪዎቻቸውን ለመለየት ሲቸገሩ ይስተዋላሉ። ወዳጅ ከሚሏቸውም ጋር የትብብራቸው መጠን እስከምን ድረስ እንደሆነ በግልጽ የተወሰነ ጉዳይ ስለሌለ እከሌን ከሚባለው ድርጅት ጋር ተባብረን መሥራት አለብን ወይስ የለብንም የሚያስነሳው ጠብ ድርጅትን እስከማፍረስ ሊያደርስ ይችላል።

በሌላ በኩል ደግሞ ሌሎች ድርጅቶች በስውርም ሆነ በግልጽ በሚያደርጉት ጣልቃገብነት አንድ ድርጅት ሊበጠበጥ ይችላል። ይህ ኢትዮጵያ ውስጥ በጣም የተለመደ ነው። ድርጅቶችን በማበጣበጥ ወያኔን የሚያህል እስካሁን የለም።

## ክብራትና ክቡራን

ግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ ወደፊት መናጥ ከደረሰበት በክብርና ሞገስ ለመፍታት የመጀሪያው ኢትዮጵያዊ ድርጅት ሊሆን ይችላል ብዬ እገምታለሁ። ግንቦት 7 እንዲህ ዓይነት ወቅት ሊመጣ እንደሚችል አስቀድሞ በማወቅ እራሱን እያዘጋጀ ያለ ድርጅት ነው። ከሁሉ አስቀድሞ አፍራሽ የሆኑ የተካረሩ ቅራኔዎች እንዳይፈጠሩ የመከላከያ ዘዴዎችን ቀይሶ በሥራ በማዋል ላይ ያለ፤ ዘመናዊ አደረጃጀቶችን ለመማር ፈቃደኛ የሆነ ድርጅት ነው። ይህ የዛሬ ውይይትም የዚህ አመላካች ነው።

ከላይ የዘረዘርኳቸው (1) የአባላት ተክለሰውነት፣ (2) የአባላት የእርስ በርስ ግኑኝነት፣ (3) የድርጅቱ ርዕይ፣ ተልዕኮና ግቦች፣ (4) የድርጅቱ ደንቦችና መመሪያዎች እና አፈፃፀማቸው፣ እና (5) የድርጅቱ የውጭ ግኑኝነት ተግባራት አንድን ድርጅት ችግር ውስጥ ሊጥሉ የሚችሉ ቅራኔዎች መመንጫ አካላት ናቸው። እነዚህ ጉዞ ከመጀመሩ በፊትና በጉዞም ተደጋግመው ሊፈተሹ እንደሚገቡ የመኪና አካላት ለምሳሌ ጎማ፣ ፍሬቻ፣ መብራት፣ ፍሬን፣ የዘይት መርጫ፣ የነዳጅ ማስተላለፊያ እና የመሳሱትን አድርገን እንያቸው። ከእነዚህ ውስጥ የአንዳቸው መሰናከል ጉዞውን ሊያስተጎጉል እና የአደጋውን መጠን ሊያበዛው ይችላል። ግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ ይህንን በቅድሚያ አውቆ እየተንቀሳቀሰ ያለ ድርጅት ነው።

ግንቦት 7 ተልዕኮውን ለመወጣት የሚያስችለውን ድርጅታዊ ጥንካሬ በምርምሮች በታገዘ መንገድ መገንባት ይኖርበታል። ለዚህም እያንዳንዱ የግንቦት7 ሕዋስ ቅራኔዎችን በአግባቡ ማኔጅ የሚያደርግበትን ክህሎት ሊያዳብር ይገባል። እያንዳንዱ ሕዋስ ራሱን የሚከተሉትንና መሰል ጥያቄዎችን መጠየቅ ይኖርበታል።

- በሕዋሳችን አብሮ የመጓዝ ችግር ያለበት ማነው? ችግሩ ከምን የመነጨ ነው?
- የትኞቹ ነገረ ጉዳዮች /issues/ ግልጽ አይደሉም?
- የትኞቹ ነገረ ጉዳዮች ቅሬታን ይፈጥራሉ?
- ሕዋሳችን በአሁኑ ሰዓት እምን ደረጃ ላይ ነው ያለው?
- ሕዋሳችንን ለቅራኔ የሚያጋልጡ ጉዳዮች አሉ ወይ?
- በአባላት የግል ፍላጎትና በጋራ ፍላጎቶቻችን መካከል ያለውን ተቃርኖ
- እንዴት ልንፈታ እንችላለን?
- አምስቱ ቦታዎች ላይ ትኩረት ሰጥተን መከላከያ አበጅተናል?
- እያንዳንዱ አባል ምን ያህል ጊዜና ጉልበት በቡድን ሥራ ላይ ያውላል?
- የእያንዳንዱን አባል የግል ችሎታና ፈጠራ በአግባቡ ተጠቅመንበታል ወይ?

(ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## እስከዛሬ ድርጅቶቻችን ውጤታማ ለምን አልሆኑም? ከገጽ 3 የዞረ

የግንቦት 7 ሕዋሳት ሰፋ ያለ ነፃነት ያላቸው አሃዶች ናቸው። ሕዋሳቱ ኃላፊነታቸውን በአግባቡ ሲወጡ እና አፍራሽ ለሆኑ ቅራኔዎች የማይመቹ፤ ተግባር ላይ ያተኮሩ ሲሆኑ መላው ንቅናቄዓችን በአስተማማኝ መለዋወጫዎች የተገነባ መኪና እናደርገዋለን።

በዚህም መሠረት ንቅናቄዓችን ከሕዋሶቹ ጀምሮ ራሱን ከአፍራሽ ቅራኔዎች የሚከላከልበት ሥርዓት እያበጀ ነው።

1. የአባላት ተክለሰውነት ተመርኩዘው ሊመጡ የሚችሉ ቅራኔዎችን ለመከላከል ድርጅታችንንና ራሳችንንም የእድሜ ልክ ተማሪዎች በማድረግ ዘወትር ግንዛቤዓችንና ክሎቶቻችንን ለማዳበር እንጥራለን። የተዛቡ ግንዛቤዎች እንዳይኖሩን ደግሞ ህይወት ያለው ውይይት የምናካሄድባቸው መድረኮችን ለማቋቋም ጥረት እያደረግን ነው።
2. የአባላት የእርስ በርስ ግኑኙነትን ተመርኩዘው ሊመጡ የሚችሉ ቅራኔዎችን ለመከላከል የአባላት ሥነምግባር መርሆዎች ወጥተው ተሰራጭተዋል። እነዚህ የሥነ ምግባር መርሆች በቅርቡ በታተመው መጽሃፍ ውስጥ ተካትተው አባሎቻችን ባልሆኑ ኢትዮጵያዊያንም እንዲታወቁ አድርገናል። የግንቦት7 አባላት በእነዚህ የሥነምግባር መርሆዎች የታነፁ መሆን ይጠበቅባቸዋል። የግንቦት 7 አባል ከዘረኝነት የፀዳ መሆንና በዜጎች እኩልነት የሚያምን መሆን እንዳለበት በመርሆዎቹ ተደንግገዋል። በዚህም ምክንያት በአባላት ምልመላ ወቅት እነዚህ መርሆዎች ከመመዘኛዎቹ ዋነኞቹ ናቸው። ከዚህም በተጨማሪ ግንቦት 7 እነዚህን እሴቶቹን ወደ ድርጅታዊ ባህል ደረጃ ለማሳደግ ጥረት ያደርጋል።
3. የንቅናቄዓችን ርዕይ፣ ተልዕኮና ግቦች በተመለከቱ ቅራኔዎች እንዳይነሱ በማያሻማ ሁኔታ በመሥራች አባላት ውይይት ዳብረው በመላው አባላት ልቦና እንዲሰርፁ እየተደረገ ነው።

ለማስታወስ የግንቦት7 ርዕይ የሚከተለው ነው

*የግንቦት 7 ንቅናቄ፣ እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ሰብዓዊ መብቱ የተከበረበት፣ የኢኮኖሚ ብልጽግናና ማኅበራዊ ፍትህ የሚያገኝበት፣ የዜጎች ሕይወት፣ ደህንነትና ጥቅም የተከበረበት ሃገር እንዲኖረው ማድረግ ነው።*

ተልዕኮው ደግሞ የሚከተለው ነው

*የግንቦት 7 ቀዳሚ ተልዕኮ የመንግሥትና የፓለቲካ ሥልጣን በሠላማዊና ዲሞክራሲያዊ ሂደት የሚያዝበትንና የሃገሪቱ ዜጎች ምርጫ በተግባር የሚገለጽበትን ብሄራዊ ፓለቲካዊ ሥርዓት እንዲገነባ ማገዝ ነው።*

ይህን ተልዕኮ በደንብ የተገነዘ ሰው ግንቦት 7 በዓይነቱ ልዩ የሆነ የፓለቲካ ኃይል መሆኑ ይገነዛባል። ከሁሉም በላይ ግንቦት 7 የተቋቋመው የመንግሥትን ሥልጣን ይዞ ሕዝብን ለማስተዳደር አይደለም። በዚህም ምክንያት የኔ ፓሊሶች የተሻሉ ናቸው እያለ ብሎ ክርክር የሚገጥምበት ምክንያት የለም፤ ለዚህ የሚሆኑ ፓሊሲዎችም የሉትም። ግንቦት 7 የሚታገለው የመንግሥት ሥልጣን በሰላማዊና ዲሞክራሲያዊ መንገድ የሚያዝበትን ሥርዓት መገንባት ነው። የግንቦት 7 ተልዕኮ ኢትዮጵያን መምራት እንፈልጋለን የሚሉ ፓርቲዎች ፍላጎታቸውን በነፃነት ለሕዝብ ዳኝነት አቅርበው የሚመረጡት ሥርዓት ማቆም ነው።

ይህን ሥርዓት የማቆምን ትግል እኔ መምራት አለብን ወይም ኃላፊቱ የኔ ብቻ ነውም አላለም። ግንቦት 7 ተልዕኮውን ተግባራዊ የሚያደርገው ከመላው የኢትዮጵያ ሕዝብና ከኢትዮጵያዊያን ድርጅቶች ጋር በመተባበር እንደሆነ ያምናል። ለዚህም ነው ተልዕኮው ይህንን የሕዝብን ትግል ማገዝ የሆነው።

በመጨረሻም ከሌሎች የፓለቲካ ፓርቲዎች በተለየ መንገድ ግንቦት 7 እንደ ፕሮጀክት የመጠናቀቂያ ጊዜ አለው። እንደ ፕሮጀክትም ውጤቱ በቀላሉ መለካት የሚችል ነው። ተልዕኮዓችንን አጠናቀቅን የምለው በዲሞክራሲያዊ ምርጫ የመጀመሪያው መንግሥት ተመርጦ ሥራውን የጀመረ እለት ነው።

ከዚህም በተጨማሪ የረዥምና የአጭር ጊዜዓት እቅዶችን አውጥተን መንቀሳቀስን እየተለማመድን ነው። በእቅድ መመራት ሥራን ከማቀላጠፍም ባሻገር አባላት በየጊዜው በሚቀያየሩ የፓለቲካ ንፋሶች ምክንያች ትኩረታቸው እንዳይዛነፍ ይረዳል ብለን እናምናለን።

4. የድርጅቱ ደንቦችና መመሪያዎች አፈፃፀም በተመለከቱ ቅራኔዎች እንዳይነሱ የድርጅት ደንቦችና መመሪያዎች ከመውጣታቸው በፊት ግልጽና ሰፊ ድጋፍ ያላቸው መሆኑን የማረጋገጥ ሥራዎች ይደረጋሉ። ደንቦች ያለ አድልዎ ተፈፃሚ ይደረጋሉ።
5. በዚህም ረገድ ሥራዎቻቸንን በደንቦችና መመሪያች መሠረት ለመሥራት ጥረት እያደረግን ነው። ከስብሰባ ሰዓት አከባበር ጀምሮ እስከ ሪፖርቶችን በወቅቱ እስከማቅረብ እንዲሁን የአባልነት ግዴታዎችን በአግባቡ እስከመወጣት ድረስ ያሉት ጉዳዮችን ሥርዓት ለማስያዝ ጥረት እያደረግን ነው።
6. የድርጅቱ የውጭ ግኑኝነትንም በተመለከተ ግንቦት 7 ከሌሎች ድርጅቶች ጋር ስለሚኖረው ግኑኝነት ግልጽ የሆነ መስፈርት አዘጋጅቷል።

ግንቦት 7

- የኢትዮጵያን ሉዓላዊ አንድነት፣
- የፖለቲካ ሥልጣን፣ በሃገር አቀፍ ይሁን ከዚያ በታች በሚገኙ አስተዳደራዊ አሃዶች ውስጥ የሚያዘው ዜጎች በእኩልነት በሚሰጡት የአንድ ሰው አንድ ድምጽ ሥርዓት መሆኑን፣ እና
- የትብብሩ የትግል ዓላማ ሥልጣን ለመያዝ ሳይሆን ሥልጣን በሕዝብ ፈቃድ የሚያዝበትን ነፃና ዴሞክራሲያዊ ሁኔታ ለማመቻቸት መሆኑን ከተቀበሉ ኃይሎች ሁሉ ጋር ተባብሮ ለመሥራት ዝግጁ ነው።

### ክብራትና ክቡራን

ለዘመናት ከኢትዮጵያዊያን የፓለቲካ ድርጅቶች ያጣነውን ድርጅታዊ ጥንካሬ ግንቦት 7 ለማምጣት ጥረት እያደረገ ነው። በንቅናቄው ውስጥ ቅራኔዎች ቢነሱ እንደእስከዛሬው መራኮትና መበታተን ሳይኖር በቅራኔዎች ጎልብቶ የመውጣት አቅምን እያዳበረ ያለ ድርጅት ገንብተናል ብዬ አምናለሁ።

ይህ ማለት ግን ሁሉም ነገር ተስተካክሏል ማለት አይደለም። ከድርጅት አንፃር ግንቦት 7 የሚቀሩት በርካታ ነገሮች አሉት። ከእነዚህ ውስጥ ዋና ዋናዎቹን ጠቅሼ ንግግሬን ልጨርስ። ድርጅታዊ ብቃትን ከማሳደግ አኳያ የሚከተሉትን በቶሎ መከወን አለብን ብዬ አምናለሁ

1. ግልጽ እና አጓጊ የለውጥ ፍላጎት በአባላት ውስጥ ማሳደር እና የአጣዳፊነት ስሜት መፍጠር፣
2. በየደረጃው ጠንካራ የሥራ አስፈፃሚ መኖር እና የአባላት ጽናትን ማጎልበት፣
3. ተስማሚ ድርጅታዊ መዋቅር መፍጠር እና የክትትል ሥርዓት ማበጀት፣
4. የአባሎቻቸንና የሕዋሶቻችንን አቅም ገንብተን ለለውጥ ማዘጋጀት፣
5. የአጫጭር ጊዜ ድሎችን እየፈጠርን መጠናከር እና ለትላልቅ ለውጦች መዘመት፣
6. ድርጅታዊ ባህል እና የለውጥ ሂደት ተደጋጋፊ እንዲሆኑ ማድረግ፣
7. አካባቢን የመመዘን ችሎታችንን ማሳደግ፣ እና
8. እርስ በርሳችም ከሕዝባችንም ጋር ያለንን ሁሉን ዓቀፍ ግኑኝነት ማጠናከር።

እነዚህ ጊዜ የማይሰጣቸው ተግባራት ናቸው።

የግንቦት 7 አደረጃጀት ወያኔን ለማስወገድ ብቃት ያለው ድርጅት ከመፍጠርም አልፎ ዘለቄታ ያለው ጠቀሜታ አለው። ግንቦት 7 ጠንካራ ሕዝባዊ ድርጅቶች እንዴት መገንባት እንዳለባቸው በሞዴልነት ልንጠቀምበት የምንችለው ተቋም ይሆናል ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ። ይህ ድግሞ ለዘላቂ አብሮነታችንና እድገታችን ሁነኛ ግብዓት ነው።

### ክብራትና ክቡራን

እስከዛሬ የኢትዮጵያ ፓርቲዎች መለያ ባህሪይ የሆነው መሰነጣጠቅ እና ወይም መሳነፍ ሳይደርስበት ዓለምነው ቦታ ሊያደርሰን የሚችል ድርጅት ተፈጥሯል ብዬ አምናለሁ። **ይህም ግንቦት7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ ይባላል።** ይህ ንቅናቄ ምሉዕ አይደለም። ሆኖም እየታገለ የሚማር፤ እየተማረ ደግሞ የሚታገል ድርጅት ነው። እስካሁን ያልተቀላቀላችሁን ካላችሁ ዛሬውኑ ተቀላቀሉን። ተባብረን ወያኔን አስወግደን በምትኩ ፍትህ፣ ነፃነትና ዲሞክራሲ የሰፈነባት ኢትዮጵያን እንገንባ!!

ስላዳመጣችሁኝ አመሰግናለሁ።

**አፕሪል 10 ሙኒክ ላይ የቀረበ ንግግር**

## የዘረኛው ወያኔ አገዛዝ ባለስልጣናት አዲሱ ለገሰና . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

በተመሳሳይ መልኩ ይህ የአዲሱ ለገሰ ቡድን ሚያዝያ 20 ቀን የጓንጓ ወረዳ መምህራንን በቻግኒ ከተማ በመሰብሰብ ስለ ምርጫና ከዚህ በፊት ስለተከናወኑ የልማት ተግባራት በሚል ሰበብ ለማናገር ሲሞክር ከተሰብሳቢዎቹ ፍጹም ዝምታ እንደገጠመው ታውቋል። በዚህ የተደናገጡት ሰብሳቢዎችም ዝምታው የጸረ-ሰላምና ጸረ-ልማት ሃይሎች መገለጫ ነው በማለት መምህራኑን ዘልፈዋል።

ከተሰብሳቢዎቹ ምንም ንግግር ሳይደረግበት በተበተነው በዚህ ስብሰባ ላይ ተሳታፊ ከነበሩ መምህራን ውስጥ አንዱ፣ የህዝባቸውን የኑሮ ችግር በቅርብ እንደሚያውቁና ወያኔ ቢያሻው ድምጻቸውን እንደለመደው በጠብመንጃ አፈሙዝ ይውሰደው እንጂ በፈቃዳቸው እንደማይመርጡት ሲናገሩ ተደምጠዋል።

**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ**
**የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።**
**በ 7140፣ 7175፣ 7185 KHZ በ 41 ሜትር ባንድ** እና **በ 6100 KHZ በ 49 ሜትር ባንድ**

ላይ ዘወትር ማክሰኞ፣ ሐሙስ እና ቅዳሜ ከጠዋቱ 3:00 ሰዓት እስከ 3:30፤ እንዲሁም ከምሽቱ 2 ሰዓት እስከ 2:30 የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ በስልክ ወይም በኢሜል በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።

**ውድ አንባቢዎቻችን**
**ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታስቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዮን ክፍላችን ዎይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን።** g7radio@ginbot7.org